# ሠ ላ ም !!

ከአቤ ኮስትሬ

እኔና ሠላም በእሳቤዬ ውስጥ ተሟግተን
መፍትሔ ይገኝ እንደሁ በሚል ተወያይተን
መልሷን ሳላገኝ ቢታክተኝ !
ትዕግሥቴ በዝቶ አስጨነቀኝ
ይኸው ምሬቴን ሕዝብ ይስማኝ !
ሠላም በመጨከኗ ብቻ እንዳልሆነም ችግሩ
አስተውላችሁ መርምሩ !
ተስማምተን ማደር ባለመቻላችን !
በመከፋፈላችን !!
ከሀገር ይልቅ ለግላዊ ጥቅም በማደራችን !!
ከ21ኛው ክፍለዘመን እሳቤ በመውጣታችን !
በዘር ጎሣዊ ስሜት በመናቆራችን !
እኔም አንተም እሷም ናት !
ሠላምን ያሳደድናት !!
ችሎታው በጃችን ነው መልሰንም ልናመጣት !!

አንቺ ኩሩ እመቤት ውበትሽ ያማረ !
የሚመኝሽ ሁሉ ሊያገኝሽ ሞከረ
ብቅ እልም ስትይ እንደ ጠዋት ጤዛ
ከሚያገኝሽ ይልቅ የሚጓጓሽ በዛ !
የሌሊት ሕልም ሆንሽ የቀኑ ምኞት
ፍጡር የሚያሳምን አለሽ ወይ ምትሃት ?
ዓለም ሲተራመስ ባይኖርሽም ደንታ
የዋሁ ፍጡር ግን አርጎሻል መከታ !

አንዳንዱም በስምሽ ምሎ ይገዘታል
ሠላም ሠላም ብሎ ወንጀልን ይሠራል !
ውበት ቁመናሽም ሰው እያታለለ
በፍቅርሽ መስጎብ ስንቱ ነሆለለ !
አጠገቡ ያለሽ እየመሰለው !
ሠላም ሠላም ይላል አወይ ሞኙ ሰው !
ብልጡማ ነግዷል ስምሽን እየጠራ !
ፍቅርሽን አጥፍቶ ወንጀል እየዘራ !

እንዲያው ለመሆኑ ሰውን ያስጠላሽ
ፍቅርሽ በራድ ሆኖ እንዲህ ያራቀሽ
በሰው ልጅ ክፋት ነው በፍላጎትሽ ?
ንገሪን ዕውነቱን ካልተሰለቸሽ
መቼም ሁሉ ክፉ ሁሉም ደግ አይደለም
ከሰውም ሰው አለ ከጎንሽ የሚቆም
ለክፉዎች ሳይሆን ለደጎች ብለሽ
ጨርሶም ሳትጠፊ ፊትሽን ብትመልሺ
አንቺን ተተግነን እንኖር ነበረ
ጥላቻሽ ርቆ ፍቅርሽ ከሠመረ

በተለይም አሁን በቅጽበቱ ዘመን
አለማወቅ ጠፍቶ ሥልጣኔ ሲገን !
የአጥፊ ጠፊ መድረክ ሆና ምድራችን !
አለን እየሠጋን ዘወትር ተሳቀን !
በአውዳሚ መሣሪያ በሚያሰቀቀው
አንዱ ካንዱ ልቆ ሮጦ ሲቀድመው
ታዲያ በዚህ ሥጋት በአስፈሪው ዘመን
እንዴት እንኖራለን ፍቅርሽ ርቆብን ?

በውዝግብ መድረክ በጥይት ሁካታ !
በተንኮል ግርግር በወንጀል ድንፋታ !
ሥርዓተ አልበኝነት ሠፍኖ በዓለም ላይ
ባለጡንቻው ልቆ ከሕግ በላይ !
የደካማው ጩኸት ታፍኖ በጦር !
በደምና እንባ ተጨማልቃ ምድር !
ለዕውነት የቆመ ፈራጅ ዳኛ ጠፍቶ !
ግፍ የተዋለበት ሰው መሆኑን ጠልቶ
ንጹሃን አልቅሰው ግፈኛው ሲዝናና
ፍጡራን ተሳቀው ዓለም እንዲህ ሆና
አንቺ እየራቅሽን በማን እንጽናና ?

መልካም ጠረንሽን ያለማመድሻቸው
አለሁ አለሁ እያልሽ የደባበስሻቸው !
በተለይ ሕፃናት አሳዛኝ ፍጡር !
እየተነፈሱ ያንቺኑ ዓየር !
ሜዳ ሲቦርቁ ደስታ ተሰምቷቸው
ሠላም ሠላም ሲሉ በጣፋጭ ዜማቸው
ይገርመኝ ነበረ አንቺን ማመናቸው !
ሠላም አንቺ ጠፍተሽ ሚሳይል በላቸው !!

እስከመቼ ይሆን የምትኮሪው ?
በጣም እየራቅሽን የምትኖሪው
ኒውትሮን ሃይድሮጂን ቀድሞሽ ሳይፈነዳ !
ያመነብሽ ፍጡር በግፍ ሳይጎዳ
በዚያ በክፉ ቀን በድድቅ ጭለማ
አንቺም እንዳትወድሚ ድምጽሽ ሳይሰማ
እንዲያው ከንቱ ሆነሽ ሠላም ከምትጠፊ !
ከዚህ ትውልድ ጋር ኑሪ ሳትከፊ
ከመጪውም ትውልድ ሽሽትሽ ይገታ !
ዓለማችን ትዳን ከኒውክሌር ፍንዳታ !
ዓለም እንዳልሆነች ሆና ከምትቀር
እጅሽን ዘርጊለት ለመላው ፍጡር !!
ሠላም አለች ይበል መሳቀቁ ይቅር !!
አንቺን ተተግኖ በደስታ እንዲኖር !
የፍጡራን ፍቅር ይሁንልሽ ደስታ !
ሠላም ለዓለም ሁሉ ሁኝለት መከታ !! አሜን !